የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ ሀምሌ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.33
ADDIS ABABA, 23rd July, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/፪ሺ፲፫

የካፒታል ገበያ አዋጅ…………………..ገጽ ፲፫ሺ፫፻፴፭

## Content

Proclamation No.1248 /2021

Capital Market Proclamation …..........Page 13335

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/ ፪ሺ፲፫

## የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የካፒታል ገበያ አዋጅ

ካፒታል በማሰባሰብ፣ የገንዘብ ስርዓቱን በአዳዲስ ፈጠራዎች በመደገፍ እና የኢንቨስትመንት ስጋቶችን የመጋራት አሰራርን በማስፋፋት የአገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት የሚደግፍ የካፒታል ገበያ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ እና ገበያው ፍትሃዊ፣ ተአማኒ እና ቀልጣፋ እንዲሆን የሚያስችል የቁጥጥር እና በበላይነት የመከታተል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣

ከሕዝብ ካፒታል ለመሰብሰብ የሚፈልጉ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጭዎች የሚገዙበትን ወጥ የሆኑ መስፈርቶች በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

በሀገሪቱ የፋይናንስ ስርዓት ላይ የሚፈጠሩ መዋቅራዊ ስጋቶችን ለመለየት፣ ለመከላከል፣ እና ለመቀነስ በካፒታል ገበያ ላይ ጠንካራ የቅርብ ክትትል እና የቅኝት ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣

## PROCLAMATION NO. 1248 /2021

## THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA CAPITAL MARKET PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to establish a capital market to support the development of the national economy through mobilising capital, promoting financial innovation, and sharing investment risks;

**WHEREAS,** it is necessary to adopt a legal framework for the regulation and supervision of the capital market to ensure the fairness, integrity, and efficiency of the market and protect investors;

**WHEREAS,** it is necessary to legislate uniform requirements for the regulation of issuers who desire to raise capital from public investors;

**WHEREAS,** it is necessary to adopt a legal framework for effective monitoring and surveillance of the capital market to detect, mitigate, and prevent systemic risk to the country's financial system;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው አዋጅ ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/፪ሺ፲፫›› ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **‹‹ማስታወቂያ››** ማለት፡-

ሀ) በጽሁፍ፣ ማስታወቂያ በመለጠፍ፣ ወይም በሰርኩላር ወይም በሌሎች ሰነዶች፤

ለ) በፎቶግራፎች፣ በሲኒማቶግራፊ ፊልሞች ወይም ቪዲዮ አውደ-ርዕይ፤

ሐ) በድምጽ ስርጭት፣ በቴሌቪዥን፣ ወይም ቀረጻዎችን በማሰራጨት፤ ወይም

መ) እንደ ድረ-ገጽ እና ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ባሉ ሌሎች ኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ብዙሃን መድረኮች፤

የሚተላለፉ ማስታወቂያዎችን ያካትታል፤

፪/ **‹‹ተሿሚ እንደራሴ››** ማለት በባለስልጣኑ የንግድ ፈቃድ የተሰጠውን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ በመወከል ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት የሚያከናውን ሰው ነው፤

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as “Capital Market Proclamation No.1248/2021.”

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ **“Advertisement”** includes every form of advertising, whether:

a) in a publication, by the display of notices or by means of circulars, or other documents;

b) by the exhibition of photographs, cinematograph films or videos;

c) by way of sound broadcast, television, or by the distribution of recordings; or

d) other electronic media platforms such as websites and social media;

2/ **“An Appointed Representative”** means a person who conducts regulated activities and acts as an agent for a capital market service provider licensed by the Authority;

፫/ ‹‹**በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች**›› ማለት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሆነው የሚያስገኙት የገንዘብ ፍሰት በዋናነት ተለይተው በሚታወቁ የተሰብሳቢ ወይም ሌሎች የገንዘብ ሰነዶች፣ ቋሚ ወይም ተዘዋዋሪ የሆኑ፣ በውል በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ገንዘብ የሚለወጡ፣ በተጨማሪም እነዚህን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለያዛቸው ሰው የሚከፈለው ገንዘብ በወቅቱ እንዲፈፀም ለማረጋገጥ ዋስትና የተደረጉ ማንኛውም መብቶች ወይም ሌሎች ሃብቶች፣

ለ) አክሲዮኖችን ወይም ከጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች የሚገኙ መብቶችን ሳይጨምር ነገር ግን የተስፋ ወረቀቶችን ጨምሮ ማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣

ሐ) ሊሸጡ እና ሊለወጡ የማይችሉ ሰነዶችን ሰብስቦ እንዲሸጡ እንዲለወጡ ወይም በራሳቸው ለግብይት የማይውሉ ሰነዶች የግብይት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መፍጠር ሂደትን ተከትሎ በተቋቋመ ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም ሃብት ላይ ከሚጠራቀም ዋና ብድር ወይም ወለድ፣ ገቢ፣ የካፒታል ክፍፍል ወይም ክፍያዎች ወይም በእነዚህ ተቋማት ላይ ድርሻ የያዙ ባለሃብቶች ማንኛውም መብት ወይም ጥቅም፣ የዕዳ ሰነድ ወይም ህጋዊ የአላባ ተጠቃሚነት ወይም በድርሻ ላይ የጥቅም መብቶችን የሚያረጋግጡ የምስከር ወረቀቶች፣ ወይም

መ) ሌላ ማንኛውም በሀብት የተደገፈ ሰነደ ሙዓለ ነዋይ አይነት መብት፣ ጥቅም ወይም ሰነድ፤

፬/ ‹‹**ባንክ**›› ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ ስራ እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም በመንግስት ባለቤትነት ስር ያለ ባንክ ማለት ነው፤

3/ **"Asset-Backed Securities (ABS)"** means:

a) securities that are primarily serviced by the cash flows of a discrete pool of receivables or other financial assets, either fixed or revolving, that by their terms convert into cash within a finite period of time, plus any rights or other assets designed to assure the servicing or timely distributions of proceeds to the security holders;

b) any securities including promissory notes but do not include shares or entitlements under a collective investment scheme;

c) any rights or interests, debentures or certificates evidencing the legal, equitable or beneficial interest or entitlement of its holder to a share of the assets of a special purpose vehicle or to entitlement to payment from such assets where payments or distributions of capital, income, principal or interest to investors accrue principally from the assets of the special purpose vehicle as a consequence of the establishment or operation of a securitization transaction; or

d) any other right, interest, instrument of security or class of securities prescribed to be asset-backed securities;

4/ **"Bank"** means a company licensed by the National Bank of Ethiopia to undertake banking business or a bank owned by the government;

፭/ **‹‹የካፒታል ገበያ››** ማለት እንደ አክሲዮን፣ ቦንድ፣ ተዛማጅ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም እነዚህን የመሰሉ የተለያዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የሚደረግበት ገበያ ነው፤

፮/ **‹‹የካፒታል ገበያ ተዋናዮች››** ማለት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች፣ ኢንቨስተሮች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ ተገቢነት ያላቸዉን ዉሎች ያደረጉ ብቁ የሆኑ ተጓዳኝ ወገኖች እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያዎች ናቸው፤

፯/ **‹‹የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ››** ማለት ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ስራዎች ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

፰/ **‹‹ማዕከላዊ የክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ወገን››** ማለት፡-

ሀ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይቶች ላይ ድህረ ግብይት የማጣራት እና ክፍያ የመፈጸም ስራን፣ እና

ለ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተገበያዮች መካከል የተቃራኒ ወገን ስጋትን የመውሰድ ስራን የሚመለከት ነው፤

፱/ **‹‹ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት››** ማለት፡-

ሀ) ከተማከለ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አያያዝ ጋር በተገናኘ፡-

(፩) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወጥነት ባለው መንገድ የሚከማቹበት፣ ወይም ወደ ኤሌክትሮኒክ ይዘት ተቀይረው የሚቀመጡበት፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በአውጪው ኩባንያ ወይም በአውጪው ኩባንያ ስም ሆኖ በሚሰራ ሌላ ኩባንያ ስም የሚመዘገቡበት ሆኖ እነዚህ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን

5/ **“Capital Market”** means a market where securities such as shares or equities, bonds, derivatives, or other related securities are bought and sold;

6/ **“Capital Market Participants”** means capital market service providers, issuers of securities, investors, securities exchanges, eligible counter parties to eligible contracts, and securities depository and clearing companies;

7/ **“Capital Market Service Provider”** means any person engaged in regulated capital market activities and services under this Proclamation;

8/ **“Central Clearing Counterparty”** refers to the act of:

a) providing post-trade clearing and settlement services for transactions in securities; and

b) taking on counterparty credit risks between parties to such a transaction;

9/ **“Central Securities Depository”** refers to a system:

a) for central handling of securities;

(1) where securities are immobilized or dematerialised and held in custody by, or registered in the name of the company or its nominee company for depositors and dealings in respect of these securities are effected by means of entries in securities accounts without the physical delivery of

በተመለከተ የሚደረግ ግብይት ሰነዶቹን በአካል ማረካከብ ሳያስፈልግ የሰነዶቹ መተሳሰቢያ መዝገብ ላይ ብቻ በሚደረግ ወጪና ገቢ ለማስተላለፍ የሚያስችል ስርዓት፣ ወይም

(፪) በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ሂደት ወቅት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ፣ ክፍያና እና ርክክብ ያለ አካላዊ ቅብብል ለማከናወን የሚያስችል ወይም ግብይቱን የሚያሳልጥ ዘዴ ወይም ስርዓት፤ እና

ለ) ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ድጋፎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሰጥ ስርዓት ነው፤

፲/ **‹‹የመዝጊያ ማቻቻያ››** ማለት በሁለት ሰዎች መካከል በተደረገ ስምምነት ዉስጥ ያሉ የተወሰኑ ድንጋጌዎችን ተፈጻሚ ማድረግ ሆኖ፦

ሀ) ሌላኛውን ወገን በተመለከተ ግዴታን ባለመወጣት የሚከሰት ሁኔታ ወይም ሌላ የውል ማቋረጫ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም በውሉ በተመለከተው መሰረት በአንዳንድ ሁኔታዎች ወዲያውኑ ሊከሰት ወይም አንዱ ሰው ለሌላው ሰው በሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ሊጀመር የሚችል፤እና

ለ) የሚከተለው ውጤት ሲኖረው፤

(፩) ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ወይም ግንኙነት እና ተገቢነት ባላቸው ውሎች ላይ በሚነሱ ወይም በተያያዙ ማናቸውም አሁን ወይም ወደፊት የሚከፈሉ ክፍያዎች ወይም የማስረከብ መብቶች ወይም ግዴታዎች ሲቋረጡ፣ ሲጣሩ እና / ወይም ሲፋጠኑ፤

(፪) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ለ(፩) መሰረት የተቋረጠን፤ ሂሳቡ የተጣራን ወይም የተፋጠነን እያንዳንዱን መብትና

certificates; or

(2) which permits or facilitates the registration, clearing and settlement of securities transactions or dealings in securities without the physical delivery of certificates; and

b) that provides other facilities and services incidental thereto;

10/ **"Close-Out Netting''** means the operation of a set of provisions in an agreement between two persons that:

a) may be commenced by notice given by one person to the other person upon the occurrence of an event of default with respect to the other party or other termination event or that may, in certain circumstances, occur automatically as specified in the agreement: and

b) has the following effect:

(1) the termination, liquidation and/or acceleration of any present or future payment or delivery rights or obligations arising under or in connection with one or more eligible contracts;

(2) the calculation or estimation of a close-out value, market value, liquidation value, or